13. ተቀባይነት እና የማስረጃ ክብደት

1/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች በማንኛውም የሕግ ሂደቶች ተቀባይነት አላቸው፤ እንደ ማስረጃም ያገለግላሉ::

2/ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የማስረጃ ክብደት ሲመዘን

(ሀ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ የመነጨበት፣ የተከማቸበት ወይም ከሙኒኬት የተደረገበት አግባብ አስተማማኝነት፣

(ለ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ይዘት ሳይቀየር የቆየበት መንገድ አስተማማኝነት፣

(ሐ) የመልዕክቱ አመንጪ ተለይቶ የታወቀበት መንገድ፣ እና

(መ) ፍርድ ቤት አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያስቀምጣቸው ሌሎች እውነታዎች ግምት ውስጥ ይገባሉ::

14. <u>ማስቀመጥ</u>

1/ በሕግ ሰነዶች፣ መልዕክቶች እና ኢንፎርሜሽን እንዲቀመጡ ግዴታ ከጣለ በሕግ የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተሟላ የሚቆጠረው

(ሀ) በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ውስጥ የሚገኝ ኢንፎርሜሽን ተደራሽ እና በቀጣይ ለማመሳከሪያነት መዋል የሚችል ከሆነ፣

(ለ) ኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ በተቀረጸበት፣ በተላከበት፣ በደረሰበት ጊዜ በመነሻ የነበረውን ይዘት ጠብቆ ከቆየ ወይም የመልዕክቱ ይዘት ያልተለወጠ መሆኑን ማሳየት የሚቻል ከሆነ፣ እና

(ሐ) የኤሌክትሮኒክ መልዕክቱ ላኪና ተቀባዩን፣ የተላከበትን ወይም የደረሰበትን ቀንና ሰዓትን ማወቅ የሚያስችል ከሆነ ነው::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) በተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎች ዙሪያ ሶስተኛ ወገኖች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች እንደ በቂ ይቆጠራሉ::

3/ ሕግ ወረቀትን ማዕከል ያደረጉ ሰነዶችና መረጃዎች ለተወሰኑ ዓመታቶች እንዲቆዩ የጣለው ግዴታ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተጠቀሱ ሰነዶች፣ መዝገቦችና ኢንፎርሜሽን ላይ ተፈጻሚ ነው::

4/ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ሰነዶች፣ መልዕክቶች ወይም ኢንፎርሜሽን እንዲቀመጡ የተጣለው ግዴታ መልዕክቶችን ለመላክ ወይም ለመቀበል ሲባል ብቻ ጥቅም ላይ በዋሉ መልዕክቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም::

5/ የኤሌክትሮኒክስ መልዕክቶችን ማስቀመጥን በተመለከተ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል::

15. <u>ቅጅ እና አጻጻፍ</u>

1/ በሕግ ሰነዶች ከአንድ በላይ በሆኑ ቅጂዎች መቀመጥ፣ መቅረብ፣ መላክ ወይም መሰጠት አለባቸው በማለት ከደነገገ፤ ሰነዱ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ከተቀመጠ፣

(ሀ) ማንኛውም የፌዴራል መንግሥት ሕግ የሚወጣው በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ ነው፤

(ለ) ማንኛውም የፌዴራል እና የክልል ሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚ፣ እና ተርጓሚ እንዲሁም ማንኛውም ሰው በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጣ ሕግን የመቀበል ግዴታ አለበት፤

(ሐ) የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ የሚታተመው በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ነው፤ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ የአማርኛው የበላይነት ይኖረዋል።

3/ ማንኛውም ሕግ በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣበት ቀን ሕጉ የታተመበት ቀን እንደሆነ ይቆጠራል።

4/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ እና በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ መካከል የሕትመት ቀንን አስመልክቶ ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ ቀድሞ በታተመው ጋዜጣ የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል።

37. <u>የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ መቋቋም</u>

1/ የፌዴራል የሕግ ጋዜጣ የሆነ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2/ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

(ሀ) ማንኛውም የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት የሚያወጧቸው መመሪያዎች፣ አመላካች መመሪያዎች፣ ማስታወቂያዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶች የሚወጡት በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ነው፤

(ለ) ማንኛውም የፌዴራል እና የክልል ሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚ፣ እና ተርጓሚ እንዲሁም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ የሚወጣ ሕግን የመቀበል ግዴታ አለበት፤

(ሐ) የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ የሚታተመው በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ነው፤ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ የአማርኛው የበላይነት ይኖረዋል።

3/ መመሪያዎች፣ አመላካች መመሪያዎች፣ ማስታወቂያዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶች በፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ታትሞ የወጡበት ቀን ሕጉ የታተመበት ቀን እንደሆነ ይቆጠራል።

4/ የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብን ቴክኒካዊ ጉዳዮች ያስተዳድራል።

5/ በንዑስ አንቀጽ (4) የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ይችል ዘንድ፣ የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት የሚያወጧቸውን መመሪያዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶች ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት የወረቀት እና የኤሌክትሮኒክ

